# የዩኤስኤ - ሐዋይ ግንኙነት ታሪክ

**እኤአ 1826 - ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ፣ የሐዋይ ኪንግደም ሉዓላዊና ነጻ አገር መሆኗን ተቀበለች።**

**እኤአ 1893 – የዩኤስ ባሕር ኃይል ለዩናይትድ ስቴትስ ደህንነት ሲባል ነው በሚል ሰበብ ሐዋይን በኃይል የያዘ ሲሆን የዩናይትድ ስቴትሱ ሚንስትር የአሜሪካንን ባንዲራ ሐዋይ ላይ ከፍ አድርገው በማውለብለብ ሐዋይ በዩናይትድ ስቴትስ ሞግዚትነት እንደምትተዳደር አወጁ። ከዚያም የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት የሐዋይዋን ንግሥት ሊሊዩካላኒን ሥልጣን አስለቀቃቸው።** (**የንግስቲትን ተቃውሞ በተመለከተ** [http://www.kanakamaolipower.org/history.php](http://www.kanakamaolipower.org/history.php) **የሚለው የድረ-ገጽ አድራሻ ላይ ማንበብ ይችላሉ።**)

**እኤአ 1898 – ዩናይትድ ስቴትስ ከዚያ ቀደም ሲል ሊዊዝያና፣ ፍሎሪዳ፣ ቴክሳስ እና ሌሎች ክልሎችን ከግዛቷ ጋር ስትቀላቅል ሲደረግ የነበረውን የመቀላቀል ስምምነት ችላ በማለት“በኦፊሴል” ሐዋይን ከግዛቷ ጋር ቀላቀለቻት። በዓለም አቀፍ ሕግ መሠረት ለመቀላቀል የተደረገ ስምምነት ከሌለ የተቀላቀለው አገር ሉዓላዊነት አይሻርም።**

**እኤአ 1959 – ዩናይትድ ኦፍ አሜሪካ የሐዋይ ሕዝብ በሞግዚትነት መተዳደሩን ይመርጠው እንደሆነ ለመጠየቅ ድምጸ ውሳኔ የሚሰጥበትን ዝግጅት አደረገች። የድምጸ ውሳኔው ውጤት እነርሱ የሚፈልጉት እንዲሆን ሲሉ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር እንዲኖር ግድ የሚለውንና የሐዋይ ሕዝብ ነጻነት ይፈልግ እንደሆነ የሚጠይቀውን ሦስተኛ ጥያቄ ሳያካትቱት ቀሩ።** 10,000 **ከሚሆኑት ሐዋይ ከሰፈሩት የአሜሪካ ጦር አባላት ባገኙት ተጨማሪ የድጋድ ድምጽ አብላጫውን ድምጽ በማግኘት ሐዋይን ሃምሳኛዋ ግዛት አድርገው ቀላቀሉ።**

**እኤአ 2015 - ሐዋይ ዛሬም የአሜሪካው ተስፋፊ ኃይል በቅኝ ከያዛቸው ቦታዎች ሁሉ እጅግ ውቧ ቦታ ስትሆን ዩኤስኤ ዛሬም ነጻነት ፈላጊውን የሐዋይ ሕዝብ እንደያዘች ትገኛለች። ሆኖም እስከመቼ** …?

***አሜሪካውያን በየዕለቱ “የዓለማችን ታላቅ ብሔር!” እንደሆኑ ይለፍፋሉ***
***አልፎ ተርፎም ልጆቻቸውን በትምህርት ቤት የታማኝነት ቃል ሲያስገቧቸው፡ “…ነጻነትና ፍትሕ ለሁሉም!”እያሉ ያስተምሯቸዋል***

***ታሪክ የሚያረጋግጠው ግን፡ ሐዋይ አሜሪካ እንዳልሆነችና ጨርሶ ልትሆንም እንደማትችል ነው!***

---

***ይህ ከሌሎች ነጻነት ፈላጊ ብሔራት ጋር ምን ተዛምዶ አለው? ብዙ ተመሳሳይነት አለው። በዓለም ላይ በኃይል የተያዙ ጥቂት አገሮች ነጻነታቸውን ለማግኘት እየታገሉ ነው። ወራሪው ኃይል ዓለም አቀፍ ሕጎችን እንዴት እንደጠመዘዘና እንደያዛቸው የሚገልጽ የየራሳቸው ታሪክ ይኖራቸዋል። የሐዋይ ሕዝብ በዓማጺው የካዋይ ደሴት ላይ ቋሚ የሆነ ትምህርታዊ ኤግዚቢሽን በማካሄድ ከዓለም ዙሪያ ለሚመጡ ጎብኚዎች ታሪካቸውንና ባንዲራቸውን ማሳየት ይፈልጋል። እርግጥ ይህ ጽሑፍም ኢንተርኔት ላይ ይፋ ይደረጋል እንዲሁም በሌሎች ብዙ ቋንቋዎች ይተረጎማል።***